ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org
ፕሮግራም፡ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ
Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band

***የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ***
***ቀን ሚያዚያ 7 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ***

## እንኳን ዶሮ የለም ሸሮ !

መላው የኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተክርስቲያን ተከታይ ኢትዮጵያውያን ምዕመናን ባለፈው ሳምንት እሁድ፤ ሚያዚያ 12 ቀን የትንሣዔን በዓል አክብረዋል። እኛም የደስታ መልዕክታችንን አስተላልፈናል። ዛሬም በድጋሚ የመልካም ምኞት መልዕክታችንን ማስተላለፍ እንወዳለን፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን ሦስቱም ታላላቅና ነባር ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ዜጎች ያሉባት መካነ- ምዕመናን ሀገር ነች። እነኝህ ሦስት የጥንት ሃይማኖቶች ምዕመናን የቶራ፤ የቅዱስ መጻሐፍና የቅዱስ ቁርዓን አማኞች በመሆናቸው፤ የመጽሀፍ ሕዝቦች ተብለው ይጠራሉ። በአንድ መለኮት ስለሚያምኑ፤ በመካከላቸው ተፈቃቅረው እንዲኖሩ እንጅ፤ እንዲጣሉ አይፈቀድላቸውም። ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ ከጥንት ጀምራ፤ ሦስቱን ምዕመናን አቅፋ የኖረች ሀገር ነች። ይህም ገፅታዋ ከአፍሪካ አህጉር ብቻ ሳይሆን፤ ከመላው ዓለም ጭምር የተለየች ሀገር ያደርጋታል ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ይህንን ስንል፤ ከዓለም ሀገሮች ሁሉ፤ ኢትዮጵያ የተለች ሀገር ነች የሚል ከንቱነትን ለማንፀባረቅ ሳይሆን፤ ሦስቱም ታላላቅ ሃይማኖቶች ምዕመናን፤ በፍቅር፤ በመተባበርና በመከባበር፤ ነጻ ዜጎች ሆነው ያሳላፉ ናቸው የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ብቻ ነው ። ይህንን ደግሞ፤ ማንም ሊያስተባብለው አይደፍርም። ፓርቲያችን፤ ለሃይማኖት ነፃነትና ዕኩልነት የሚታገለውም፤ ከዚህ መሠረታዊ ሀቅ በመነሳትም ጭምር ነው። በሃይማኖት ሊያምኑ ያልፈቀዱ ዜጎቿም፤ በነጻነታቸው ተከብረው የመኖር መብታቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ እንዳልሆነ እናምናለን።

እነኝህ ሦስት ነባር ሃይማኖቶች፤ በየበኩላቸው፤ ለኢትዮጵያ ነፃነትና ኅልውና፤ የተጫወቱት አዎንታዊ ሚና ነበራቸው። አሁንም አላቸው። በማኅበራዊ ኑሮ፤ በሥነ ምግባርና በሥነልቦና በኩልም አሻራው፤ ምንጊዜም የማይደበዝዝ ማህተም አስቀምጠዋል። በቋንቋና በሥነጽሁፍ፤ በትምህርትና በሥልጣኔም ዓይነተኛ አስተዋጾ አድርገዋል። ይህም በበኩሉ፤ ለኢትዮጵያ ማንነትና ለዜጎቿም ምንነት አረጋጋጭ ነው። ለሀገራችን ነባርነትና ጥንታዊነትም ህያው ምስክሮች ናቸው። " ***ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የተፈጠረችው የዛሬ አንድ***

***መቶ ዓመት ነው "*** ለሚሉት ከንቱ ፍጡራንም ዋጋ እንዳይኖራቸው አድርገዋል። ፀረ ኢትዮጵያ ዓላማቸውም ከሽፎ ቀርቷል።

የሀገሪቱ የፖለቲካ መሪዎችና የውጭ ባዕዳን፤ እነኝህን ጥንታውያን ሃይማኖቶች ለየራሳቸው መጠቀሚያ ለማድረግ ብዙ ሙከራ ከማድረግ የተቆጥቡበት ጊዜ አልነበረም። የኦቶማን ግዛት፤ የአውሮጳ ቅኝ ግዛት አስፋፊዎች፤ እንግሊዞች፤ ጣሊያኖች፤ ግብጾችና ድርቡሾች፤ በየተራና በመተባበር፤ ሃይማኖቶቹን ለራሳቸው ዓላማ ማስፈጸሚያ ለማድረግ ሞክረዋል። ሁሉም አልተሳካላቸውም። ጉዳት አላደረሱም ማለት ግን አይቻልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የሁሉንም እንዳመጣጣቸው፤ የመከፋፈል ተንኮላቸውን እየመከተ አክሽፎ፤ አንድነቱን ጠብቆ በነፃነቱ ኖሯል።

የሀገር ውስጥ አምባገነኖቹም በበኩላቸው፤ በሃይማኖት የውስጥ ጉዳይ በመግባት፤ የከፋፍለህ-ግዛ ፖሊሲያቸውን ለመጠቀም ያልተቆጠበ ጥረት አድርገው ነበር። እነርሱም አልተሳካላቸውም። ዛሬ ግን እጅግ ሲበዛ የከፋ ሥርዓት ሰፍኗል። በሃይማኖት ብቻ ሳይሆን፤ በቋንቋና በጎሳም ጭምር እየከፋፈለ ለመግዛት የወያኔ አገዛዝ ይዳከራል። የዚህ ዕኩይ ሥርዓት የከፋፍለህ ግዛ ተግባር ያስከተለው አንደምታ በቀላሉ የሚገመት ባይሆንም ቅሉ፤ ሕዝቡን ፈጽሞ ለመከፋፈል ግን አልሆነለትም ። በጽኑ መሠረት ላይ አንድነቱ የተገነባ ሕዝብ፤ በቀላሉ እንደማይጠፋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ህያው ምስክር ነው።

ወያኔ፤ አንድ ያልተገነዘበው መሠረታዊ ሀቅ ቢኖር፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ባኅርይና ልምድ፡ ረቂቅነትና የኅብረተሰቡንም ውስብስብነት ፈጽሞ አለመረዳቱ ነው። *" ኢትዮጵያ መልኳን፤ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይተዋል እንዴ ? "* የሚለውን ሃይማኖታዊ ቃል መገንዘብ በተገባ ነበር። ይህ ግን ከወያኔ የሚጠበቅ አይደለምና በጥፋት መንገድ መጓዙን ቀጥሎበታል። እርሱ እየከሰመ ይጠፋል እንጅ ኢትዮጵያን ግን እንደማያጠፋት፤ ሕዝቡ በሰማይና ምድር ቃል ገብቷል። የሕዝብ ቃለ መሃላና ውሳኔ ደግሞ መፈፀሙና መከበሩ አይቀርም ። ሁሉም ዜጋ፤ ለዕድሜው ዕድሜ ይስጠው !

ሀገራችንን በቋንቋ፤ በጎሳና በሃይማኖት መከፋፈል ያልሆነላቸው የውጭና የውስጥ ባላንጣዎች፤ ርዕዮትን መሠረት ያደረገ ከፋፋይ መሣሪያ ለመጠቀም ሞክረዋል። በታሪክ፤ ሀገራችን ለተለያዩ የመጠቀሚያ ስልቶችና የአገዛዝ ሥርዓቶች፤ ቤተ- ሙከራ ( ኤክስፐሪመንት ) ሆና ቆይታለች። ኢትዮጵያን፤ ልክ ለሳይንስ ምርምር መፈተሻ ፤ በላቦራቶር ውስጥ እንደሚበለት እንስሣ መሞከሪያ አድርገው ተጠቅመውባታል ። ሕዝቡንም ለሙከራቸው መፈተሻ አድርገውታል። በተለይ በቅርቡ

የተፈራረቁት ደርግና ወያኔ  እንደ ማስረጃ ይጠቀሳሉ። ደርግ ባልገባውና ባልተረዳው ርዕዮት ውስጥ እየዳከረ፤ አንዱን እያነሳ ሌላውን እየጣለ፤  ሀገሪቱንና ሕዝቡን የመፈተሻው መጫወቻ አድርጎታል። ሶሻሊዝምን አመጣለሁ ብሎ ፋሽዝምን አስፋፋበት። ሙከራው አልሆን ሲለው፤ ሀገሪቱን ለሌላ ቤተ ሙከራ ተለማማጅ አስረክቧት ወደ እሚሄድበት ሄደ።

ወያኔም በበኩሉ፤ " የብሄሮች እስር ቤት ነች " የሚላትን ሀገር፤ የብሄሮች ቤተ-ሙከራ ሊያደርጋት መጣ። የኢትዮጵያንም ሕዝብ በዘርና በቋንቋ ለመከፋፍል እንዲመቸው፤ የአጥንትና  የደም ምርመራ ላቦራቶሪ የሚያካሂድበትን የየክልል  ቤተ ሙከራ አስፋፋ።

የአንዱን ብሄር ደምና ኣጥንት ከሌላው ብሄር  ደምና ኣጥንት ሊለይ የሚያስችለውን  ውጤት ለማግኘት ነበር። የቤተ-ሙከራው መስፋፋት ግን የፈለገውን ውጤት አላስገኘለትም። **ምክንያቱም፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ አንዱ ከሌላው ጋር፤ በአጥንት በስጋው፤ በደሙና በጎዋሱ የተገናኘ፤ የተዛመደ፤  ተጋብቶ የተዋለደ፤ ተዋኅዶና ተወሳስቦ በአንድነት የኖረ በመሆኑ ነው።**

ማነኛውም ኢትዮጵያዊ አባቱንና እናቱን ከጠራ በኋላ፤ ከፍ እያለ የዘር ሀረጉንና የትውልድ አመጣጡን እያጠቀሰ ሲሄድ፤ ካንዱ ወይም ከሌላው ብሄረሰብ ጋር እንደሚዘነቅና አያት ቅድመ አያቱን ከሌላው ብሄር ብሄረስብ ጋር ተዘናንቆ ያገኛዋል። ይህም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ሀረገ-ብዙ፤ ዘርፈ ብዙና ፈርጀ ብዙ አድርጎት ኖሯል። ወደፊትም ይኖራል።  ለዚህም ነው የወያኔ የዘር ፌዴራሊዝም  ከንቱ የሚሆነው። የማይሰራው። ሕዝብን፤ በዘርና በደም የመከፋፈል ምርመራ የጀርመን  ናዚዎቹም አካሄደው አልተሳካላቸውም ። በሂደቱ ግን በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ አልቋል። በሀገራችንም፤  የወያኔ ዘረኛ ፌዴራል አገዛዝ፤ በአመጣው ጣጣ፤ ስንት ንፁሃን  ዜጎች እንዳለቁ ቁጥራቸው ተመዝግቦ ተቀምጧል።

ለዚህም ነው፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ  ለማስተዳደርና ለመምራት፤ በቤተ- ሙከራ  የሚደረግ  መፈተሻና በቀዶ ጥገና የሚሰፋ ጥብቆ የማይመጥነው። የማይስማማው። የማይሆነው። ታዲያ፤ መፍትሄው ምንድን ነው? ተብሎ ሲጠየቅ፤  መልሱ፤ ገደብ-የለሽ  የዴሞክራሲ ሥርዓት ሰፍኖ፤ ሕዝቡ የራሱን አስተዳደር ራሱ መስርቶ፤ የራሱን ውሳኔ ማድረግ አለበት የሚል ነው።  እኔ አውቅልሃለሁ የሚለው፤ የማታለያ ዘመን ካከተመ   ዘመን አልፏል ። ወያኔ ግን፤ የደረቀ  ወንዝ ተሻጋሪ፤  የሞተ ፈረስ ጋላቢ ከሆነ ቆይቷል። ክፉ መካሪዎቹም ወደ ገደል አፋፍ እየገፉት ይገኛሉ።

ለፖለቲካ ሥልጣን መያዣ ሲባል፤ ደርግና ወያኔ ሀገሪቱን ቤተ-ሙከራ ሊያደርጓት ሞከሩ። ጎልቁ-መሳፍርት፤ ማለትም፤ ብዙ ጥፋት አደረሱ። ጥፋቱ አሁንም ቀጥሏል። ማባሪያው መቸ እንደሚሆን ግን ማንም በዕርግጠኝነት መናገር የሚችል አልተገኘም ።

እነኝህ ጥንታውያን ሕዝቦች፤ ሁሉ እያላቸው ሁሉንም ያጡ ሆነዋል ። የበለጸገ ታሪክና ባኅል፤ መሠረታቸው ጥልቅ የሆነ ሃይማኖቶች የሰፍኑባት ሀገር፤ የራሳቸው ቋንቋዎችና ፊደላት ያላቸው ዜጎች፤ ታዲያ የራሳቸውን ችግር ራሳቸው መፍታት የተሳናቸው ለምን ሆኑ ?

ለዚህ ጥያቄ፤ የተፍታታና አጥጋቢ መልስ ሊሰጥ የሚችል ያለ አይመስልም ። መልስ መስጠት እሚችል ካለ ግን፤ የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች የገባው አለ ማለት ይቻላል ። የተሟላ መልስ መሰጠት ከተቻለ ደግሞ፤ ሕዝብ ሆ ! ብሎ በመውጣት የመፍትሄው ፍለጋ ተካፋይ ይሆን ነበር። ዛሬ፤ ለብዙ ኢትዮጵያዊ እንቆቅልሽ የሆነው እኮ፤ ለችግሩ መፍትሄ ማግኘት አለመቻሉ ሳይሆን፤ ለመፍትሄ የሚስማማ ችግር መጥፋቱ ነው ተብሎ ድምዳሜ ላይ መድረሱ ይመስላል። የኢትዮጵያን ችግር በቅጡ ካልተረዱት ደግሞ፤ መፍትሄውን አግኝተነዋል ማለት የሚቻል አይሆንም። " **ኢትዮጵያ ባለ ጉራማይሌ መልክ ነች** " ማለት እኮ፤ የዜጎቿን ስብጥርነትና ኅብረ ብሄርነት እንዲሁም፤ የቁንጅናዋንም ውበት ለመግለፅ ተብሎ ነው እንጅ ፤ ጎልቆ መሳፍርትና ረጋ-ሰራሽ ቀለማት እያሳዩ በየመድረኩ መቅረብ ማለት አይደለም ።

ራዕይ ያላቸው አዋቂዎች መጥፋት፤ በተባባሪ ኃይል ጠንክሮ የወጣ የተቃዋሚ ድርጅት አለመኖር፤ ብሎም፤ አምባገነንም ቢሆን እንኳ፤ ሀገር-ወዳድ የሆነ፤ ኢትዮጵያዊ መንግሥት መጥፋት፤ የሀገራችን ሕዝብ ዙሪያው- ገደል ሆኖበታል ።

የዐርባ ቀን ዕድልን በማማረር ብቻ ጊዘያዊ እፎይታ ቢገኝማ ኖሮ፤ የዕለት-ተዕለት ችግራችንን የምናስታግስበት ፋታ እናገኝ ነበር። ግን ኑሯችን፤ ቋቱ ጠብ አለማለቱ ብቻ ሳይሆን፤ ከእጅ- ወደ አፍ የሚሆን፤ የሚላስ- የሚቀመስ አለማግኘታችን ጭምር ነው ። ይህም በመሆኑ፤ ችግረኛው ሕዝባችን----

" የዐርባ ቀን ዕድሌ ባያደላድለኝ ፤

ለምኜ እበላለሁ ሰው እንደበደለኝ ። " እያለ ዕድሜውን ይገፋል ።

ኢትዮጵያውያን ምዕመናን፤ ፆመ -አርባን በጾም በፀሎት ከሳለፉ በኋላ ፤ ለጾማቸው መፈስኪያ የሚሆን ትንሽ ጹሉላት እንኳን ማግኘት ተስኗቸዋል ። ይህም የሆነው በኑሮ ውድነት፤ በዋጋ ንረትና በገንዘብ ግሽበት ምክንያት ነው። ለአብነት የሚከተሉትን ዕቃዎች ዋጋ እንመልከት :-----

| | |
|---|---|
| ዶሮ | 280 ብር |
| በግ | 6000 ብር |
| ፍየል | 8000 ብር |
| አንድ ኪሎ ቅቤ | 220 ብር |
| አንድ ኪሎ በርበሬ | 100 ብር |
| አንድ ኪሎ የበሬ ስጋ | 220 ብር |
| አንድ ዕንቆላል | 3 ብር ከ 50 ሣንቲም ሆኗል ። |

በኢትዮጵያ ምድር ዛሬ ደሃው መኖር ስለአልቻለ፤ ወደ ኢትዮጵያ ሰማይ፤ ለሰማዩ ንጉሥ፤ የሚከተለውን ምኅላ ቀጥሏል።

" አምላከ ማረኝ ማረኝ ፈጣሪየ አትርሳኝ፤

ዶሮም ሺህ አወጣ እኔም ሥጋ አማረኝ፤

የሰማዩን መና በገፍ አዝንብልኝ

ወይ ለእኔ የሚያስብ መንግሥት መስርትልኝ

ያለዚያ ከሀገሬ፤ ከዚች ምድር አውጣኝ " ።

ይህ፤ የሕዝብ ምሬትና ለቅሶ ከተራ እምባ አልፎ ተርፎ፤ ወደ ደም እምባ እየተለወጠ ከሄደ ዓመታትን አስቆጥሯል ። የሕዝብ ጥቅም አስጠባቂም ሆነ፤ የሕዝብ እምባ ጠባቂ ምድራዊ መንግሥት ባለመኖሩ፤

ምዕመናኑ አቤቱታቸውንና ሮሯቸዉን ወደ አምላካቸው ቢያሰሙ ማንስ ይፈርድባቸዋል ? የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ነጻነቱንና ሀገሩን ለማስከበር፤ ከደም ዕምባ አልፎ ተርፎ፤ የህይወት ዋጋ እየከፈለ የቆየ ቢሆንም፤ አሁንም፤ እምባው ወደ ደም ተለውጦ የደም ዕምባ እያለቀሰ እንዲኖር ተፈርዶበታል ። እምባውን የሚያብስለት ግን ማንም እንደሌለ ከተረዳው ቆይቷል ።

ከባኅላዊ ተመክሮና ዕምነት በመነሳት፤ ዱሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ መንግሥትን ይፈራ ነበር። አልፎ አልፎም ያከብርም- ያምንም ነበር። ያ ዘመን አልፏል። ዛሬ ግን መንግሥት የሚባለውን ተቋም አያምንም። አይፈራምም ። ይህንን ያወቁ፤ አምባገነኖች ያላቸው ምርጫ አንድ ነው። በኃይል እየጨቆኑ መግዛት ! ፍትኅ ርትዕ አሳጥቶ ማንገላታት! አፍኖና አምቆ መፈናፈኛ ማሳጣት! እያሰሩ ወህኒ መከተት፤ በጅምላ መግደል ! ከሀገር ማሰደድ ! እኔን ያየህ ተቀጣ በሚል፤ ብዙሃኑ ለመብቱ እንዳይነሳ፤ በፍርሃት እንዲኖር ማድረግ! ያገዛዛቸው ስልት ነው ።

በዚህ ምክንያት ፤ መንግሥት የሚባለው ድርጅት ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ የማፊያዎቹ ፤ የአሸባሪዎችና የወንበዴዎች ጥርቃሞ ማለት ነው። በሀገሪቱ ውስጥ፤ ሁለንተናዊን ኃይልና አከማችቶ፤ ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ሥልጣንን የቋጠረ ኃይል በመሆኑ፤ የመጨቆኛ መሳሪያዎቹን ሁሉ አካብቶ በብቸኝነት ተቆጣጥሮ ይዟል ። የሀገሪቱን ሃብት በመዳፉ ውስጥ አስግብቷል ። የጦር ኀይሉን፤ ለሕዝብ ማስፈራሪያ ይጠቀምበታል ። የፖሊሱን ድርጅት፤ ጸጥታውን ይቆጣጠራል ። የሀገሪቱ ድሆች ቁጥርና የሰላዮቹ ቅጥር መሳ ለመሳ ናቸው ። ያወጣውን ህግና ድንብ የሚተረጉሙለትን ፍርድ ቤትና ዳኞች ይመድባል። የሕዝብ ማጎሪያ ወኅኒ ቤቶችን በብዛት ይገነባል። ፕሮፓጋንዳውን፤ ለማስፈራሪያና ለማወናበጃ ይጠቀምበታል። ተጠራርተውና ተጠረቃቅመው ለይስሙላ "በፓርላማው" ጋራጅ የሰበሰባቸው ጀሌዎች፤ የራሱ አጨብጫቢዎች መሆናቸውን ያረጋግጣል ። ጠቅለል ባለ መልኩ፤ በሀገራችን፤ ራሱን በመንግሥት ስም የሚጠራው ፤ እንግዲህ የዚህ ዓይነቱ የጭራቅ ድርጅት ነው ።

በዚህ ሁናቴ መንግሥትና ሕዝብ፤ ዓይንና አፍር፤ ዕሳትና ጭድ፤ አጥፊና ጠፊ፤ ሆነው ይኖራሉ ። ዘራፊና ተዘራፊ አሳዳጅና ተሳዳጅ፤ ሆነው ሳይተማመኑ፤ ዘመናት አልፈዋል። ዕምነትና መተማመን የሚባል ነገር በመካከላቸው አልነበረም። ወደፊትም ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም፤ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የማይከበሩባት ሀገር፤ የአንድ ፓርቲ ፈላጭ-ቆራጭ አገዛዝ ይንሰራፉና፤ ሙስና፤ ንቅዘት፤ ብልሹና ተስፋ ቢስ የሆኑ መሪዎች መደናበሪያ ሀገር ሆና ትቀራለችና ! ጊዚያዊው የሀገርችን ሁኔታ የዚህ ነጸብራቅ ነው ።

የቀድሞው የፈረንሳይ ፕረዝደንት የነበሩት ጀኔራል ሻርል ደጎል በአንድ ወቅት

" ማነኛውም መንግሥታዊ አቋም፤ የሀገሪቱን ግዛታዊ ዳር ድንበር ማስከበር ካልቻለና የሕዝቧንም ክብረ-ወሰን ደረጃ ካልጠበቀ፤ ያለምንም ጥርጥር ህጋዊነት ሊኖረው አይችልም ። " ብለው የተናገሩት በሚገባ የሚገልፀው ነው።

የወያኔም ሥርዓት፤ በምንም መስፈርት ቢለካ፤ ህጋዊነት የለውም። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ይህንን አውቆ ተቀምጧል ። መወገድ እንዳለበትም ድምዳሜ ላይ ደርሷል ። ይህንንም በመረዳት ነፍስ- ወከፉ ዜጋ ከመታገል በቀር ሌላ አማራጭ እንደሌለ አውቋል። በገዳም ያሉት መናንያንና መነኮሳት ሳይቀሩ፤ ወያኔን ለማስወገድ ፤ ከፀሎቱ ጋር ፤ መታገል እንደሚያስፈልግ የሚከተለውን መልዕክት እያስተላለፉ ነው ።

" ወግድልኝ ድኋ ወግድልኝ ቅኔ

ጀግኖች በዋሉበት እውላለሁ እኔ ። "

ትላንት የትንሣዔን በዓል ያከበሩት ምዕመናን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን አብዛኛዎቹ፤ በኑሮ ውድነት የተነሳ፤ በችግር ማሳለፋቸው ልባችን በሀዘን ተነክቷል። እንኳን ስጋ፤ በአዋዜ እንጀራ ያረረባቸው በሚሊዮን እንደሚቆጠሩ እንረዳለን።

" እንኳን ዶሮ የለም ሽሮ! " ተብሏል። የሀገራችንን ሁኔታ ለመለወጥ፤ የወያኔ መወገድ ፤ የመጀመሪያው ምዕራፍ መሆኑን ተረድቶ፤ ከመታገል በቀር ሌላ አማራጭ የለም ። ይህንን ምርጫን መርጦ ሁሉም እንዲተባበር እንጠራለን !

ክብር ለሰማዕታት !

ስየል የሚቀበሉትንና የፖለቲካ እስረኞችን አንረሳቸውም !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !